# የተደበቀው ድርቅ

ከበልጅግ አሊ

፩

ወይ ኑሮ! ወይ ኑሮ! ቁርንጮ! ቁርንጮ!
ወልደን ለዘመቻ፣ ሥርተን ለመዋጮ።

አስር ዓመት ሙሉ፣ ቆመን ስናናፋ፣
ከሰማይ ዝናቡ፣ ከምድር ቅጠል ጠፋ።

ቮልቮን ለደርግ አባል፣ ላዳን ላቃጣሪ፣
ይህ ነው አብዮትሽ ኢትዮያችን ኩሪ።

ቀና ብዬ ባየው ሰማዩ ቀለለኝ፤
እግዜርን ዘመቻ ወሰዱት መሰለኝ።

ቀና ብዬ ባበየው፣ ሰማዩ ቀለለኝ፣
አላህን ሰፈራ፣ ወሰዱት መሰለኝ።

የሕዝብ የብሶት ግጥሞች ።

የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ተከፍቷል። ከቀድሞ የወያኔ አባል ከነበሩት ከአቶ ገብረ መድህን ጋር ቃለ መጠይቅ ይሰማል ። “ለድርቁ የተሰጠንን ገነዘብ የጦር መሣሪያ እንገዛበት ነበር“ . . . የአቶ ገብረ መድህን ቃለ መጠይቅ ድርቁን አስታወሰኝ።

የትራክተሩ ጩኸትና በመስኮቱ በኩል የሚገባው የፀሐይ ፍንጣቂ ከእንቀልፌ ቀሰቀሰኝ። ከአልጋዬ አጠገብ በዳንቴል ተሸፍኖ የተቀመጠውን ራዲዮ ከፈትኩት። ዜና እስኪደርስ አብዮታዊ መዝሙሮች በተከታታይ ሲያሰማ የነበረው የኢትዮጵያ ራዲዮ የዜናው ሰዓት መድረሱን እንደተለመደው “እንደምን አደራችሁ“ በማለት ሰሞኑን ዐብይ ዜና በመሆን ፕሮግራሙን ባጣበበው የአስረኛው ዓመት አብዮት በዓል ዝግጅት ጀመረ። አንባቢው በተለያዩ ክፍለ ሀገሮችና ከተማዎች እንደሚደረግው ሁላ የበዓሉ ዝግጅት በኢሊባቡር ክፍለ ሃገር በመቱና በጎሬ ከተማዎችም ዝግጅቱ በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን ዘገበ።

ይህንን በተመለከተ ዛሬ ስብሰባ መኖሩን ሳስታውስ ቶሎ ተነስቼ ልብሴን ለባብሼ ለስራ በተሰጠችኝ ሞተር ሳይክል አዲስ ወደ ተተከለው ሻይ ሄድኩ። የወራቃ ክልል ካቦ የሆነው ይስማው እየተጣደፈ መጥቶ ሰላምታ ከመስጠቱ በፊት፦

“ትራክተሮቹ መቼ ነው የሚመለሱት?“ ብሎ ሲጠይቀኝ ።
“የታወቀ ነገር የለም። ጎሬ ከተማ ኢሠፓአኮ ፅህፈት ቤት ውስጥ ቆመዋል ነው የተባለው።“ አልኩት።

“ማዳበሪውን በምን እናመላልሰው? . . . . የዝናቡ ጊዜ ካለፈ እኮ ዋጋ የለውም። . . . . ባለፈው ሳምንት ነበር መረጩት የነበረበት። . . . እሺ ትራክተሮቹ እስከሚመለሱ ይገዛ የተባለው አህያ ጉዳይ ምን ደረሰ ? . . . . “

“ለአህያው በጀት የለም፣ የገንዘብ እጥረት አለ ተብሏል።“ መለስኩለት።

“ትራክተሮቹ በቅርብ ጊዜ እንደማይመለሱ የታወቀ ነው። . . . . መኪናዎቹ በሙሉ ከወሰዷቸው ሰነበቱ። . . . .ሠራተኛውን በእግር እያመላለስን ነው የምንሠራው። . . . . . የተለቀመውን ሿይ በምን እናመላልሰው? በሰው ትከሻ ምን ያህል ከባድ መሆኑን አያውቁም እንዴ? . . . . . ሠራተኞቹ በጣም ተማረዋል . . . . .“ እያለ የማውቀውን ችግር እንደ አዲስ እንደገና ያስረዳኝ ጀመር።

“ምንም ማድረግ አንችልም። መጠበቅ ብቻ ነው። የኢሠፓአኮ ኮሚቴ ነው አመራር የሰጠበት . . . .።“ መለስኩለት።

ይስማው እንደተለመደው እያልጎመጎመ ወደ ሥራው ተመለሰ። እኔም ወደ ስብሰባው ቦታ በረርኩ። ሁሉም ተሰብሳቢዎች ቀደም ብለው ተገኝተው ኖሮ እንደገባሁ ስብሰባው ተጀመረ።

የስብሰባ ሥነ ስርዓት የማያውቀውና አብዮትን የሚመለከትን ጉዳይ ብቻ ካልሆነ ሌላውን ስብሰባ ሳይጠራ በግሉ የሚወስነው የሻይ ልማቱ ሥራ አስኪያጅ ማሞ በምን አጀንዳዎች ላይ እንደምንነጋገር ሳይናገር በቀጥታ ለእሱ አንገብጋቢ መስሎ ወደአገኘው ችግር በመግባት፡

“ለአስረኛው የአብዮት በዓል ዝግጅት የተፈቀደልን ገንዘብ አለ። በአስቸኳይ አንድ ነገር ማድረግ አለብን፡“ ብሎ ድንጋጤ እያንተባተበው ስብሰባውን ጀመረ። ማሞ ሁል ጊዜ ስለ አብዮቱን ሲናገር ለደርግ ያለውን ጥላቻን ጎልቶ የሚታይበት እየመሰለው ፍርሃት ያኮላትፈዋል ።

“ለመሆኑ ምን ያህል ገንዘብ ነው የተመደበልን?“ አለና የሂሳብ ክፍል አላፊውን ጠየቀው።

በኤርትራ ተወላጅነቱ ጥርጣሬ ላይ እንዳይወድቅ ከሚገባው በላይ ለፖለቲካ ካድሬዎች ታማኝነቱን ለማሳየት የሚፍጨረጨረው የሂሳብ ክፍል ሃላፊ አብርሃ፡

“በገንዘብ በኩል ችግር አይኖርም። የተመደበው ሃምሳ ሺህ ብር ነው። ይህ ካነሰ ግን ከሌላ ወጭዎች ቀንሰን ወደዚህ ማድረግ እንችላለን።“ ብሎ መለሰ።

የሕንፃ ኮሌጅ ምርቅ በመሆኑ የሚኮራውና አብዮት ማትሪክ እንደከዘራ ጫፍ የተጣመመባቸው ካድሬዎች መሰብሰቢያ ነው ብሎ የሚያምነው የኮንስትራክሽን ክፍል ሃላፊ ዳሩነህ የሳሳ ፀጉሩን እያሳሸሸ፡

“ለሻይ ተክሉ የሚያስፈልጉ እቃዎችን እንግዛ ስንላችሁ በጀት የለም ስትሉ የነበራችሁ አሁን ይህንን ሁሉ ገንዘብ ከየት አመጣችሁት? ይህ ሁሉ ዶዘር የሃይድሮሊክ ዘይት ማስተላለፊያው ቱቦ ተበጥሶ ቅያሬ አጥቶ ብረቱ በቆመበት ሲዝግ፣ ትራክተሮቹ በመጠገኛ ዕቃ እጦት ቆመው ሲቀሩ፣ የሠራተኞች መኖሪያ ቤቶች ቆርቆሮ አርጅቶ ውሃ ሲያፈስ፣ ክኒሊኩ መድሃኒት አጥቶ ሠራተኛው በበሽታ ሲሰቃይ ምንም ባጀት ያልነበረ አሁን ለአሸሼ ገዳሜ ሃምሳ ሽህ ብር ከየት ተገኘ?! ባለፈው ሳምንት አይደለም እንዴ ለማዳበሪያ ማጓጓዣ አህያ መግዣ ቢጠየቅ በጀት የለም የተባለው? ለመሆኑ እዚህ ጫካ ውስጥ ሃምሳ ሽህ ብር ምን አድርጋችሁ ልትጨርሱት ነው? ለእያንዳንዱ ካድሬ አብዮቱን ስለደገፈ ጉቦ ትሰጡት እንደሆን እንጂ ምንም ልታደርጉበት አትችሉም። ሆ! ሆ! ሆ ! የሚገርም እኮ ነው።“ በማለት የሚያምሩ ነጫጭ ጥርሶቹን ፈገግ አደረገና ሁላችንም ተራ በተራ ይመለከተን ጀመር ።

ቀልድ ሲጀመር ደስ የሚለውና የሚያገኘውን ገንዘብ በማባከን የሚታወቀው፣ በቅርብ ከራሺያ የመጣው መኮንን፡

“ለእኔ ስጡኝና ላብቃቃው“ በማለት ለትምህርት ውጭ በነበረበት ጊዜ ለመድኩት በሚለው ሳቁ ክፍሉን አናጋው።

ስለ አብዮቱ ድክመት ከተነገረ በግል የተሰደበ የሚመስለው፣ በንግግሩ መሃል የሊቀመንበር መንግሥቱን ስም መጥራት የሚወደው፣ በቅርብ ከሌላ እርሻ ልማት ተቀይሮ የኢሠፓኮ መሠረታዊ ድርጅት ሃላፊ ሊሆን ነው የመጣው ተብሎ የተነገረለት አበራ የዳሩነህን ንግግር ሲሰማ የተቀመጠበት ወንበር ላይ መቁነጥነጥ ጀመረ። ከእጁ የማይጠፋውን የቀን መቁጠሪያ ደብተር ከፍ በማድረግ ከማሞ ፍቃድ ከጠየቀ በኋላ፡

“ጉዳዩ አሳሳቢ ነው። ይህ የአብዮት በዓል ከሌላው ልዩ የሚያደርገው ኢሠፓአኮ ወደ ሠራተኛው ፓርቲነት የሚለወጥበት ወቅት ስለሆነ ነው። ጓድ ሊቀመንበር እንዳሉት ፀረ አብዮተኞች ይህንን ጉዳይ ለማክሸፍ የማያደርጉት ጥረት የለም። የፓርውን ምሥረታ ለማክሸፍ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በሲ.አይ.ኤ እየተረዳ የማይፈነቅው ድንጋይ አይኖርም። በዚህ ወቅት እያንዳንዳችን ለአብዮቱ ዘብ መቆም ይኖርብናል። እኛም ሁላችንም ሠራተኛውን በማስተባበር የፀረ አብዮተኞችን ደባ ማክሸፍ ይጠበቅብናል!“ ብሎ ሹል የሆነ አፉን በማሻሸት የዳሩነህ ጥያቄዎች እንዳልነበሩ በማለፍ ስለ በዓሉ ትልቅነት አሳስቦ ንግግሩን አቆመ።

“ምን ዓይነት ፀረ አብዩተኛ በዚህ ጫካ ውስጥ ይገኛልና ነው አብዮቱን የምንጠብቀው? . . . አብዮተኛም ፀረ አብዮተኛም ያሉት አዲስ አበባ ውስጥ ነው።. . . . በዙሪያችን አሉት የዱር አራዊትም የመደብ ጀርባ ኖሯቸው በፀረ-አብዮተኝነት ካልተፈለጉ በስተቀር?! ከፈለግህ እዛ ሄደህ ታገል ።. . . . . እዚህ ያለው እርሻ ነው ። የሚሆን የማይሆን እያመጣችሁ ሥራ አታስፈቱን። . . . . አዲስ የተተከለው ሳይኮተኮት የዝናቡ ጊዜ ካለፈ ሻዩ እንደሚደርቅ

አታውቅም? . . . . ለዚህ ዝግጅት ብለው መኪናዎቹና ትራክተሮቹ በአውራጃው ፓርቲ ተጠሪ በጓድ ግርማ ከተወሰዱ ሳምንት አለፈው። . . . .  በሚቀጥለውም ወር የሚመለሱ አይመስለኝም።“ ብሎ ዳሩነህ ወደ ተለምደው ጭቅጭቁ ሊገባ ሲል፡ -

“አቁም! የተሰጠንን መመሪያ ማስፈፀም እንጂ በመመሪያው ላይ መነጋገር አንችልም። ስለተወሰዱት መኪናዎችና ትራክተሮች ከፈለግህ ሂድና የኢሠፓኮ የአውራጃው  ተጠሪ ጓድ ግርማ ጎሬ ይገኝልሃል እሱን ጠይቅ።“ ብሎ ማሞ አስቆመው። ማሞ በፍርሃት ምክንያት መኪናዎቹን ይስጥ እንጂ በዚህ ወቅት ምን ያህል ለእርሻው ሥራ አስፈላጊ መሆናቸውን አጥቶት አይደለም።

ከማሞ ቀበል አድርጎ  አብርሃ፡

“ጓድ አበራ ከላይ የተሰጠ መመሪያ ካለ ብትነግረን ለሥራችን አመቺ ስለሚሆን ጉዳዩን መልክ ያሲይዘዋል።“ አለ።

“እኔ የማይገባኝ ነገር አለ! የዚህ መስሪያ ቤት ሥራ አስኪያጅ ማሞ ነው ወይስ አበራ?“ ብሎ መኮንን  ጣልቃ ገብቶ በውስጥ የሚታማውን  ስብሰባው ላይ በግልፅ አወጣው። አበራ በዚህ ጥያቄ ከማሞ ጋር በመመደቡ  ተደሰተ እንጂ አልከፋውም። ማሞ ግን በንዴት ፊቱ ተለዋወጠ።  ግን ምንም ማድረግ ስለማይችል ርዕሱን ለመቀየር፡ -

“ይህንን መቾፍቱ ተውት። እባካችሁ ወደ ዋናው ቁም ነገር ገብተን እንነጋገር። ለሥራችን አመችነት  አበራ  የተሰጠ መመሪያ ካለ ንገረን“ በማለት ማሞ የመኮንንን ጥያቄ በማጣጣል አበራን መማፀን ጀመርን። <<መቾፍቱ>> ለመኮንን የተሰጠ ቅፅል ስም ነው።

አበራ ተፈላጊነቱ ስለጎላ በኩራት ተዝናንቶ፡

“ከላይ የሚመጣው መመሪያ መዋቅሩን ጠብቆ ይመጣላችኋል። ቢሆንም የተመደበውን ገንዘብ በአስቸኳይ ሥራ ላይ ማዋል ይኖርብናል።  ገንዘቡ ከተሰጠን  በኋላ መሥራት የምንችለውን አለመሥራታችን ያስጠይቀናል። የተለያዩ ዝግጅቶች ማስተባበር ከኛ ይጠበቃል። ይህንን በተመለከተ የሠራተኛው ማሕበር አመራር ይሰጠዋል።  ለምሳሌ በግቢው ውስጥ በዓሉን በተመለከተ አደባባይ መሥራት እንችላለን።“ ብሎ ሃሳቡን ሳይጨርስ፤ ዳሩነህ ከት ብሎ ስቆ፡

“አደባባይ ! . . .እዚህ ጫካ ውስጥ ! . . .  ምንኑ ጋ ነው የምንሰራው ?“ አለና መልስ በመፈለግ  ሁላችንም በየተራ እየተመለከተ ይጠብቅ ጀመረ። ማንም የሚናገር ሲጠፋ ማሞ፡

“እባክህ ዳሩነህ አትረብሸን፣ መሥራት ካለብን እንሠራለን። አሁን ግን አበራ መናገር ይቀጥል።“ አለ።

“ይህ መመሪያ ነው። . . . ውይይት የሚደረግበት አይደለም። . . .  ሥራ ከተባልክ ትሠራለህ። . . .  እንቢ ማለት አትችልም። . . . . እኔ እኮ ተባብረን እንወያይበት ብዬ ነው እንጂ ከአውራጃው የኢሠፓአኮ ቢሮ መመሪያ ማሰጠት እችላለሁ። አብዮቱ ላይ አንዳንድ ግለሰቦች ሲያላግጡ ዝም ብዬ ማየት አልችልም። . . . “ ብሎ  አበራ ዳሩነህ ላይ ዓይኑን  አጉረጠረጠ። ዳሩነህ አበራን፡

“ስማ ሁሉንም ልትጠይቅ ትችላለህ። . . . ሥራን በሚመለከት ለእኔ ተወው። . . .  እንዳንተ ተቀምጬ አይደለም የምውለው። . . . . ግን መጀመሪያ በምሠራው ጉዳይ  እኔን ማሳመን አለብህ።  ይቺ ሀገር የእናንተ ብቻ አደለችም። እዚህ የመጣኸው አመረር ልትሰጥ ከሆነ ሌላ ነገር ነው። መመሪያ ስጥበትና እንሥራው እንጂ ስብሰባ እያልክ ልባችንን አታውልቅ“  ብሎ እሱም አመረረ። ዳሩነህ ጎበዝ ሠራተኛ መሆኑን የታወቀ ሲሆን የክፍለ ሃገሩ የኢሠፓአኮ ተጠሪዎች ምንም እንኳ የፖለቲካ አቋሙን በሚመለከት ብዙ ወሬ ቢሰሙም እስከ አሁን ሊተናኮሉት አልፈለጉም።

ማሞ፡

“አደባባይ መሥራት አንድ ነው። ሌላስ ምን ማድረግ እንችላለን?“ ብሎ አበራን ጠይቆ ዳሩነህን ከእንግዲ አቁም በሚል ለስላሳ ግልምጫ ገሰፀው።

አበራ ማሞ ስለደገፈው ተዝናንቶ፡

“ሌላው በአካባቢያችን ምንም እንኳ የሚያስፈራ ጉዳይ እስከ አሁን ባይኖርም ጥበቃ መደረግ አለበት። በሻይ ፋብሪካው አካባቢ ጥበቃና  በጉመሮ ወንዝ ድልድል ላይ  ኬላ ተደርጎ የሚተላለፉ መኪናዎችን መፈተሽ ይኖርብናል።“ ብሎ ሳይጨርስ፡ -

“ታውቃለህ ከሙቱ እስከ ጎመሮ ባለው 30 ኪሎሜትር ውስጥ ስንት ኬላ እንዳለ? በየትንሹ ጅረት ላይ የተሠራውን ድልድይ ለመጠበቅ ኬላ አቋቁመን መፈተሽ ከጀመርን እስከ ጋምቤላ ድረስ ያለው መንገድ በመኪና ከመሄድ በእግር ሊቀል ነው ማለት ነው . . .“  ብሎ የተለመደ ሳቁን  መኮንን ቀጠለ።

ባይሣ  በቅርብ ለእረፍት ሄዶ ከአዲስ አበባ የተመለሰ ስለነበር በየመንገዱ የተመሰረተው ኬላ ብዛትና  የፍተሻ አሰልችነቱን ከገለፀ በኋላ ቢሆንም ግን ጥበቃ መደረግ ካለበት የበላይ አመራር ተጠይቆበት መመሪያ እንዲሰጥበት ያስፈልጋል በማለት ተናገረ። ባይሣ የሻይ ፋብሪካው ክፍል ሃላፊ ሆኖ የሚሠራ ሲሆን ማሞ በአብዮቱ ላይ ባለው ችግር ምክንያት ከሥራ አስኬያጅነቱ ቢባረር  በቦታው ለመተካት ከኢሠፓኮ ጋር መወዳጀት ከጀመረ ሰንብቷል።

“ይህ ልከኛ አባባል ነው። ምን አልባት ሁኔታውን ማሳመን የምንችለው  የቀኑን ፍተሻ ትተን በሌሊት ጥበቃ ላይ ብናተኩር  ይሻላል“ ብሎ አበራ ተጨማሪ ሰጠ።   በባይሣና በአበራ መካከል መቀራረብ መጀመሩን የተመለከትን ተጠቃቅሰን አሽሟጠጥን።

“እዚህ ጫካ ውስጥ  በሌሊት የትኛው መኪና ሊመጣ ነው? በሌለ ሰው ላይ ሳይሆን በዱር አራዊቱም ላይ ሰዓት አ ኢላፊ ልናውጅ ካላሰብን በስተቀር? ... “ብሎ ዳሩነህ እንደገና ጣልቃ በመግባት ጥያቄ ቢያቀርብም ለማንኛውም የሌሊቱ ጥበቃ መደረግ አለበት  በሚል ቤቱ ተስማምቶ አጀንዳው ተዘጋ።

አብርሃ ከፍርሃቱ የተነሳ በእሱ ሃላፊነት ስር ያለው የሃምሳ ሺህ ብር ሳንጠቀምበት ብንቀር የሚያስጠይቀው ስለመሰለው በመቸኮል፡

“የተመደበልንን በጀት እንዴት እንጠቀምበት?“ ብሎ ጥያቄ ዳግመኛ አቀረበና የጀመርንበትንና የተረሳውን ዋናውን አጀንዳ አንቀሳቀሰው።  እንደተለመደው ዳሩነህ በችኮላ፡

“በጥበቃው ከተስማማን የሌሊት ጠባቂዎችን እንክፈላቸዋ !?“ አለ።

“ሁሉም ወዛደር ለአብዩቱ ዘብ መቆም አለበት እንጂ ለሚያደርገው ተሳትፎ በንዋይ ሊደጎም አይገባም።“ . . .  ብሎ ጀመረ የንድፈ ሃሳብ ብስለቱንና ማገናዘቡን ለማሳየት - አበራ። ቀጠለና “ . . .  ስለ ሌሊን ሶቦትኒክ አታውቁም እንዴ? ሶቪየት  ሕብረት በነበርኩበት ጊዜ የሶቪየት ሕዝብ ሃገሩን ለመገንባት ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይል በትርፍ ጊዜ ምርትን ለማሳደግ፣ አብዮቱን ለመጠበቅ ያደረገው ተጋድሎ ተመልክቻለሁ። ታዲያ ዛሬ አብዮታችን ከፀረ አብዮተኞች ጋር ፍጥጫ በገጠመበት ጊዜ ስለ ክፍያ ማሰብ ከአንዳንዶቻችን የማይጠበቅና ወደፊት ይህ አባባል ቢደገም ሊያስጠይቅም የሚችል መሆኑን ማወቅ ይኖርበናል። . . . .“ በማለት በመቆጣት አጉረጠረጠ። አበራ ለፖለቲካ ትምህርት ለስድስት ወር ሶቪየት ሕብረት መሄዱን ለማሳወቅ በተገኘው ርዕስ ላይ ሁሉ ሳይጠቅሰው አያልፍም።

አብረሃ ሲፈራ ሲቸር ዳሩነህን መደገፉ እንዳይሆን እየተጠነቀቀና ስለበጀቱ ሳይወሰን ስብሰባው እንዳይበተን በመፍራት፡

“የተሰጠንን በጀት በሥራ ላይ መዋል ይኖርብናል። የዳሩነህ ጥረት ለዚህ ይመስለኛል እንጂ በመጥፎ አይደለም።“ ብሎ ሁኔታውን ለማለሳለስ በዚያውም  ሃላፊነቱ ላይ የተኛውን ገንዘብ ማስጠጊያ መንገድ እንዲፈለግ አሳሰበ።

መኮንን እንደገና አሁንም እንደለመደው በችኮላ፡

“አበራ መመሪያ ይስጥበት እንጂ እኛ ምን አለፉን! . . . “ አለና እየሳቀ ቀልድ ለበስ ሀሳቡን አቀረበ ።

ማሞ መኮንን ትቶ አበራን እየተመለከተ፡

“በዚህስ በኩል ምን ልትረዳን ትችላለህ?“ በማለት  ጠየቀው ።

“በዚህ ገንዘብ ይህ ስብሰባ የፈለገውን ሊወስን ይችላል። እንደ አንድ ተሰብሳቢ የማቀርበው ሃሳብ ቢኖር ከአውራጃው ለጉባዔ የሚሄዱትን የምሣ ግብዣ ማድረግ እንችላለን።“ብሎ አበራ ሳይጨርስ፤ ዳሩነህ፡

“እነሱስ ሶቦትኒኩ አይመለከታቸውም እንዴ?“ ብሎ የማሾፍ ሳቁን ቀጠለ።

“ለአንተ ሳይሆን ለቤተሰብህና ለልጆችህ ስል አሁን ይቅርታ አደርግልሃለሁ። በኢሠፓኣኮ ወደፊትም በኢሠፓ አባላት ላይ የምታደርገውን ማሾፍ ካላቆምክ ይህንን ስብሰባ ጥዬ ነው የምወጣው። ከዛ በኋላ ምን በሁላችሁም ላይ

እንደሚደርስ ታውቁታላችሁ። በሠራተኛው ማካከል ተቀምጣችሁ በአብዮቱ ላይ ማሾፍ አትችሉም። የአብዮቱ በትር እንኳን እዚህ ሶማሌ ውስጥ ጠላቶቻችንን እየቀጣ ነው።“ ብሎ አበራ ዳሩነህ ላይ ሲጉረጠርጥ፡ -

ሁላችንም ችግሩ ከተካረረ የሚያስከትለውን በማሰብ “ጓድ አበራ ዳሩነህን ታውቀዋለህ። አገሩን ይወዳል፣ ታታሪ ሠራተኛ ነው፣ እንደማንም ሰው ድክመት አለው። እኛ እንመክረዋለን።“ ብለን አበረድነው ። ዳሩነህንም እረፍ ብለን አስጠነቀቅነው።

ማሞ ከኢሠፓአኮ ቁጥጥር ኮሚቴ ሊቀመንበር ጋር የነበረውን ቅራኔውን የሚያላላለት ሁኔታ ሲፈልግ ስለነበር ይህ ግብዣ የተባለው ጥሩ አጋጣሚ መሆኑን ታስቦት በሃሳብ ተውጦ የሁለቱን የጦፈ ክርክር ልብ አላለውም ነበር። ከጥቂታ ዓመታት በፊት ማሞ በችግኝ ጣቢያ ውስጥ የነበረውን ችግኝ ከመጠን በላይ ማዳበሪያ እንዲሰጠው አዞ ችግኙን አቃጥሏል ተብሎ ተወንጅሎ ክሱ ለአውራጃው የኢሠፓአኮ ተጠሪ ለሆነው ለጓድ ሶሪ ቀርቦ ነበር። ሁኔታው ግን ሲድበሰበስ ቆይቶ ማሞ ጓድ ሶሪ ለሻይ ተከላ መሬት ዝግጅት የመጡትን ዶዘሮች ለእግር ኳስ ሜዳ ዝግጅት ሲባል የ12 ሰዓት መንገድ እንዲጓዙ በጠየቀበት ጊዜ በሻይ ተክሉ ውስጥ በነበረው የሥራ ጥድፊያ ምክንያት እንቢ በማለቱ እንደገና ጉዳዩ ተንቀሳቅሶ እንደ ኢኮኖሚ አሻጥር ተቆጥሮ እሱን ጦር ፍርድ ቤት ለማቅረብ ጓድ ሶሪ ያስፈራራ ነበር። ማሞ ያቺን እንቢ ያለበትን ቀን በተደጋጋሚ ይረግም ነበር። ከዛ በኋላ ኢሠፓአኮዎቹ የሚሉትን ሁሉ ቢያደርግም ፋይሉ ግን አልተዘጋም ነበር። ዛሬ በዚህ ግብዣ ምክንያትና ሰሞኑን በሰጣቸው መኪናዎችና ትራክተሮች ምክንያት ከጓድ ሶሪና ከጓድ ግርማ ጋር ተግባብቶ ፋይሉን ለማዘጋት ብሎም በጣም የራቀውን፣ ከልቡ የሚፈልገውን፣ የኢሠፓአኮ አባልነት አገኝ ይሆን ብሎ በሃሳብ ተውጦ ነበር። በዚሁም እንቅልፍ የነሳውን የአበራን እና የባይሣን ሴራ ለማክሸፍ እንደሚረዳው አምኖበታል። ባይሣ ደግሞ ቦታውን ለመውሰድ በትምህርትና በኢሠፓአኮችም ተመራጭነት ነበረው።

ማሞ ከወሰደው ሃሳብ ሲባንን፡

“ይህ የምደግፈው ሃሳብ ነው“ ብሎ ጀመረ። “ከአውራጃው ወደ አዲስ አበባ የሚሄዱትን አባላት መጋበዝ ይኖርብናል። ምን አልባት ደግሞ ሠራተኛውንም በሌላ ጊዜ እንኳን ለፓርቲው ምሥረታ አደረሳችሁ ብለን መጋበዝ አይከፋም። ይህ ችግር የሚፈጥር አይመስለኝም።“ ብሎ የጓድ አበራን መስማማት በዓይኑ ይፈልግ ጀመር። ጓድ አበራም መስማማቱን በፈገግታ ገለፀ።

ሁላችንም በተገኘው ስምምነት ትንሽ ተረጋጋን። ዳሩነህ ግን የሁላችንንም አድርባይነት እየተመለከተ የቅሬታ ፈገግታውን ያሳየን ነበር። ብዙም ሳይቆይ አበራ ረስቶት እንደቆየ ሃሳብ፡

“በጎሬና በመቱ ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ የከፍለ ሃገሩን እድገት የሚያሳይ ኤግዚቢሽን ይዘጋጃል። በዛ ላይ ዝግጅቱን በኛ በኩል የሚሳዩ ሁለት ግለሰቦች እንምረጥ“ በማለት ሃሳብ አቀረበ። ነገሩን እንደ ቀላል ስለተመለከትነው ለክፍለሃገሩ መቱ ላይ የሻይ ተክል ኤክስፐርት የሆነውና ዕውቀቱም ያለው ተስፋዬ ይሂድ ለአውራጃው ጎሬ ላይ ግን ሌላ ይፈለግ የሚል ሃሳብ ቀረበ።

ጓድ አበራ ግን ቀድሞ አስቦበት የመጣ ስለሆነ፡

“ምህረቱ ለክፍለ ሃገሩ ቢሆን ይሻላል። ተስፋዬ ግን ሥራም ስለሚበዛበትና እዚህም ስለሚፈለግ ጎሬ ቢሆን ጥሩ ነው“ በማለት ያቀረበውን ሃሳብ ብዙዎቻችን ምክንያቱ ስለገባን ካለ ተቃውሞ አለፈ። ምህረቱ ለኢሠፓአኮ ወሬ ያቀብላል እየተባለ የሚታማ ሲሆን የኢሠፓአኮ አባል ለመሆን በጣም የሚያቀነቅን ነበር። ለክፍለ ሃገሩ ኤግዚቪሽን የተመረጠው ለፖለቲካ አመለካከቱ በሚመለከት ነው እንጂ ምንም የእርሻ እውቀት አልነበረውም። ከኢሠፓዎች ጋር ቅራኔ የማይፈልገው ተስፋዬ ቶሎ ብሎ ስለተስማማ አጀንዳው በዚሁ አለቀ።

“የመፈክርስ ጉዳይ“ በሚል ጓድ አበራ በጣም የተፈራውን አጀንዳ ስብሰባው ያለቀ መስሎን ሁላችንም ልንነሳ ስንል አነሳ ነው። መፈክር በድርብ ፅሁፍ መፃፍ የሚችለው ከመካከላችን ዳሩነህ ነው። እሱን ይህንን ጉዳይ አሳምኖ ማፃፍ አይቻልም። ሁላችንም ተጨነቅን። ማን ይጠይቀው? ማሞ ሲፈራ ሲቸር ጠየቀው። ያሰበውን መናገርን የማይፈራው ዳሩነህ፡

“መፈክሩ የሚፃፍበትን አቡጀዲ ለታረዘው ሕዝብ ስጡት። እኔ እንደሆንኩ ይህንን መፈክር ፅፌ ማንበብ የማይችለው ገበሬና ሠራተኛ ላይ አላፌዝበትም። እናንተ ፃፉት እንጂ? እናንተስ ተምራችሁ የለም እንዴ? . . .“ ብሎ የንዴት ፈገግታውን አሳይቶን ስብሰባውን ትቶ ወጣ።

አበራ መዛቱን ቀጠለ። ሁላችንም ዳሩነህን እንደምንመክረው ቃል ገብተን እስከ ነገ እንዲታገሰን ጠየቅነው። አበራ ከሄደ በኋላ ሁላችንም እንደገና ተሰብስበን ዳሩነህን እንዴት እንደምናስማማ እንመካከር ጀመር። አንድ ብልሃት መጣልን

ወዳጁና አበልጁ የሆነውን ተስፋዬ ብቻ ሊያሳምነው እንደሚችል አምነን ተሰፋዬን እንዲሄድ ጠየቅነው። ተስፋዬ ተስማምቶ ለማሳመን ወደ ዳሩነህ ቤት ሄደ። ሁላችንም የሚደርሰውን አደጋ በመፍራት መልሱን እንጠብቅ ጀመር።

ተስፋዬ  ሲመለስ ሁላችንም ጠበቅነው ። ባይሣና አበራ ግን  አልተገኙም። ምን አልባት ይህን ጊዜ ዳሩነህ ላይ ስለሚወስዱት እርምጃ ይመካከሩ ይሆናል። ተስፋዬ መስማማቱን ሲነግረን ሁላችንም ደስ አለን።

ተስፋዬ የአስራ ሰባት ዓመት ልጅ እንደነበር የደረሰበት መከራ የደረሰበትን ለዳሩነህ ተረከለት። በግርፋት ብዛት የተቆራረጡ ጣቶቹን አሳየው።. . . . .  የሕይወት ታሪኩን ለመጀመሪያ ጊዜ ከልቡ አጫወተው።  ዛሬ አብዮቱ ለአስረኛው ዓመት በዓሉ ጭዳ ይፈልጋል። ኢሠፓኮዎቹ ጠላት በሌለበት ጠላትን ይሻሉ።  አንተ ደግሞ ይህንን እያወቅክ እራስህንን ለማይሆን መስዋትነት ማቅረብህ፣ ልጆችህን አለ አባት፣ ሚስትህን አለ ባል፣ እናትህን አለ ጧሪ፣ ለማስቀረት እንደሆን እንጂ የምትለውጠው የለም። በሃገራችን እንደ ውጭ ጠላት ነው የምንታየው። ሕይወታችን በጃቸው ነች ያለችው። ሊገሉን፣ ሊተውን ይችላሉ።  . . . . . ለልጆችህ አንተ ብቻ ነው ያለሃቸው፣ ጉዳቱ ለቤተሰቦችህ ነው። እባክህ በቆሰለ ልባችን  ላይ ሌላ ሃዘን አትጨምርብን። ይህንን ብቻ እሺ ብለህ ተቀበለን። ጊዜ እስከሚያልፍ ድረስ እንዲህ መኖር አለብን። . . . . ሌላም ብዙ ነገር አጫወተው።  ከብዙ ውይይት በኋላ ተስማማ ። በሚቀጥሉት ቀናት መፈከሩ መፃፍ ተጀመረ።

የ10ኛው የአብዮት በዚያ ገጠር ሳይቀር ብዙ ገንዘብ ፈሶበት ተከበረ። የኢሠፓ አባሎች ባለ ከራባትና ሙሉ ልብስ ሆነው በውስኪ ተራጭተውበት  አለፈ። ኢሠፓአኮ ኢሠፓ ሆነ። የጦር ኃይል አባላት የነበሩት ሲቪል ሆነው በጦሩ ውስጥ የነበራቸውን ማዕረግ ትተው ሲቭል ሆኑ ። የኢሠፓ መሰረታዊ ድርጅቶች በየቦታው ይቋቋሙ ጀመር።

ግርግሩ ከአለፈ ከጥቂት ወራት በኋላ  የአውራጀው የኢሠፓ ተጠሪ ከጎሬ ሲከንፍ መጣ። ሁላችንም ሰበሰበንና ንግግር ጀመረ እንዲህ እያለ፡

“በተደጋጋሚ በዝናብ እጥሮትና በፀረ አብተኞች በተደረገብን ሻጥር ድርቅ ገብቶ ብዙ ጉዳት አድርሷል። ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ የሰሜኑ ሕዝብ ወደ ለም የሆነው ክፍል እንዲሠፍሩ ስለወሰኑ በእኛም አውራጃ በየገበሬው ማህበር ቤት ተሰርቶ ሠፋሪዎቹ እንዲሰገሰጉ ስለተወሰነ ሁላችንም ጥረት ማድረግ አለብን ። . . .“ መመሪያ ሰጥቶ መኪናውን አስነስቶ ሄደ።

ለነገሩ ነው እንጂ ስለሕዝቡ መራብ ኢሠፓዎቹ በውስኪ ሲራጩ በውጭ ሬዲዮ ጣቢያዎች እንሰማው ነበር።  ብዙ ሺህ ሕዝብ በተለይም ህፃናት በረሃብ አለቁ። ድርቁ ኢሠፓዎቹ በዓላቸውን እስከሚያከብሩ ድረስ ተደብቆ ዜጎች በሚያልቁብ ጊዜ ውስኪና የቅንጦት እቃዎች ከውጭ እየተገዙ ለኢሠፓ አባላት መዝናኛ ይውሉ ነበር።

ዳሩነህ የመቀየሻውን መሣሪያ ተሸክሞ ለሠፋሪዎቹ መንደር ለመመሥረት የሚያመች ቦታ ለመፈለግ ከእባቡና ከዘንዶ እየተጋፋ ጥቅጥቅ ወደ አለው ደን በገጀራ ቅጠሎቹን እየቆረጠ ገሠገሠ። አበራ የመሠረታዊ ድርጅት ተጠሪነቱን ለማስፈፀም ወደ ጎሬ አቀና። ማሞ ለኢሠፓ አባልነት ተመለመለ። ያ ፍቅር የሞላበት እርሻ ተቀይሮ የጌታና የሎሌ ግንኙነት ሠፈነበት።  እነ ተስፋዬም ጊዜያቸውን ጠብቀው ከሃገር ወጡ። አብርሃ በብዙ ጉቦ ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት ተቀየረ። . . . .

ይቀጥል ይሆን ?

ሰለ እኛ የሚያስብ ሁሉ በሰላም ይክረም ! ! !

Beljig.ali@gmail.com

እንደ ተጨማሪ፡ -

ድርቁ ቁጥር ሥፍር የሌለው ሕዝብ በሚያልቅበት ወቅት የኢሠፓ አባላት በውሲኪ ሲራጩ የወያኔ መሪዎች ደግሞ ለእርዳታ የመጣውን ገንዘብ የጦር መሣሪያ ይገዙበት ነበር። ለዛ ሁሉ ሕዝብ ማለቅ የኢሠፓም ሆነ የወያኔ  መሪዎች ተጠያቂዎች ናቸው። እነ መለስም ይሁኑ እነ መንግሥቱ አንድ ቀን በሕዝብ ፊት ለፍርድ ይቀርቡ ይሆን? ... ትግሉ ቀጥሏል።